# አንዳንድ ጥቅሶች ከደራሲ ሀዲስ አለማየሁ ሥራዎች

አሰናጅ፥ ፈቃደ አዘዘ

በሀገራችን ፀሀፍት ቀደም ብለው የተነገሩ ቁም ነገሮችን ወጣት በመሆናቸው እዘመኑ ላይ ተገኝተው ያላነበቡ ሰዎች አሉ። እዘመኑ ላይ ተገኝተውም የሀገሪቱ ጋዜጣዎች፥ የራድዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ለኒህ ቁም ነገሮች ተገቢውን ትኩረት ስላልሰጧቸው ያላነበቧቸው፥ ያልሰሟቸው ይኖራሉ። ዘመናዊ የሚባለው የሀገራችን ትምህርትም ባብዛኛው ወደውጭ ማየት እየተጠናወተውና እየተጫነው ስለመጣ፥ ልጆችና ወጣት ተማሪዎች የሀገራቸውን ፀሐፊዎች የሚያውቁበት፥ እንደልባቸው የሚያነቡና የሚያጠኑበት አጋጣሚ እየጠበበ ስለመጣም እኒህን ቁም ነገሮች ሊያውቋቸው አልቻሉም ብዬ አስባለሁ። ባለፉት ብዙ ዓመታት፥ በተለይም ደግሞ ባለፈው ሩብ ምዕት ዓመት (ወይም 25 ዓመታት)፥ በታወቁና እጅግም ባልታወቁ የውጭ ሀገር ደራስያን፥ የሳይንስ ጠበብት፥ ፈላስፎች፥ ምሁራን፥ ወዘተ. ተነገሩ እየተባለ የአንድና የሁለት መስመር ብሂሎች በየጋዜጣው፥ በየመፅሄቱ፥ በየቴሌቪዥኑ እና በየራድዮ ፕሮግራሙ ሲጠቀሱ የሚሰሙት ባብላጫው በዚህ የተነሳ ይመስለኛል። ለጊዜው፥ ጥያቄዬ፥ "ለምን ተጠቀሱ?" አይደለም። የዛሬው ሀሳቤ ከሀገራችን ቀደምትና ዘመነኛ ደራስያን፥ ሰዓልያን፥ "ፈላስፎች"፥ ባለቅኔዎችና ልዩ ልዩ ፀሀፊዎች ስራዎች ውስጥ የሚገኙ ቁም ነገሮችን በብዛት እየጠቀስን ብናቀርብ፥ በተለይ ወጣቱ ትውልድ እውቀትና ፍልስፍና ሁልጊዜ ከውጭ ሀገር ቋንቋና ከውጭ ሀገር ዜጋዎች ብቻ የማይገኝ መሆኑን ለመጠቆም እና፣ ብዙ ጊዜ በየብሂረሰቡ ቋንቋ በሚነገሩት ውስጥም መልካም መልካም ቁም ነገርና ረቀቅ ረቀቅ ያለ ሀሳብ መኖሩን ተገንዝቦ ከጥገኝነት አስተሳሰብ በመጠኑም ቢሆን ይላቀቃልና እንዲህ ዓይነቱን ባህል እንጀምር-እናስፋፋ-እናዳብር ለማለት ነው። ለጊዜው ከደራሲ ሀዲስ አለማየሁ ሶስት መፃህፍት የለቀምኳቸውን እና አቶ አስፋው ዳምጤ፥ አጣድፌ በጠየቅሁት መሰረት ከየልምዣት የመረጣቸውን አቅርቤያለሁ። ወደፊት ግን፥ ሁኔታው ከፈቀደ፥ በተለይ ከ1900 ዓ.ም. ጀምሮ ተፅፈው ካገኘኋቸውና በቃል ሲነገሩም ከሰማኋቸው የለቀምኳቸውን በመልክ በመልኩ ለማቅረብ አስባለሁ።

ከዚህ በታች የቀረቡት ጥቅሶች፥ በሳሎቹ የሀገራችን ደራስያን በፈጠራ ድርሰት ማራኪ ታሪክ የሚተርኩ ብቻ ሳይሆኑ የሀገራቸውን የትምህርት አኪያሄድ እያስተዋሉና እያጤኑ የሚሻሻልበትን መንገድ የጠቆሙ፣ የሀገራቸውን የአስተዳደር፥ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የሶሻል ጉዳዮችም አጢነው፥ ሀሳባቸውን ከሌላው ዓለም ሁኔታ ጋር አነፃፅረው፥ ለሀገራቸው ልማትና ብልፅግና ይበጃል፥ ከሀገራዊው አኗኗርና ልማድ ጋርም ይሰናኛል ያሉትን የስልጣኔ መንገድ

ያመላከቱ መሆናቸውን በጥቂቱ እንደሚያስገነዝቡ ጥርጥር የለውም የሚል እምነት አለኝ። ይህ እምነት ትክክለኛ ሆኖ አግኝተነው ከተስማማን፥ እንደዚህ ዓይነቱን ምርጥ ሀገራዊ የመንፈስና የአእምሮ ሀብትም እርስ በርስ የምንጋራበትንና የምንመረምርበትን መንገድ ካሰላን፥ ይህንንም ለወጣቱ ትውልድ በጭፍን ስሜት ሳይሆን በዕውቀት የምናስተላልፍበትን መንገድም ከቀየስን የአእምሮና የመንፈስ አባቶቻችንን ድካም ከንቱ ከመሆን አተረፍነው ማለት ይሆናል።

## 🕮✍ ከትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም (1948 ዓ.ም)

. . .ድርሰት፥ ሥዕል፥ ሙዚቃ የማኅበሩን የታሪክ፥ የእምነት፥ የክሕደት፥ የዠግንነት፥ የፍርሀት፥ የውበት፥ የመጥፎነት፥ የፍቅርና የመጥላት ስሜት ገልጸው ለማሳየት የሚችሉ እንደ ሆነ በዚሁ በኩል የማኅበሩን ፍላጎት ያጠግባሉ። (ገፅ 59)

. . .የኢትዮጵያ ጥንታውያን ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን በሃይማኖትና በኑሮ ሥርዐት ብቻ ወስነው የኢኮኖሚክን፥ ያስተዳደርን፥ የፖለቲካን፥ የወታደርነትን፥ የተግባረ እድንና ሎሎችንም የጥበብ ትምህርቶች ከትምህርት ሰሌዳቸው ውጭ ስለተዋቸው በሰጡት ትምህርት የማኅበሩን ፍላጎት ሊያጠግቡ አልቻሉም። እንዲሁም የኢትዮጵያ ዘመናዊያን ትምህርት ቤቶች በጥበብ ትምህርት ብቻ ተወስነው የማኅበራቸውን ታሪክ፥ የኑሮ ሥርዐት ልማዱን እንዲሁም ኢትዮጵያዊ አሰኝቶት የሚኖረውን ቅርስ ከትምህርት ሰሌዳቸው ውጭ የተዉት እንደ ሆነ ፍላጎቱ እንደሚገባ ይጠግባል ለማለት የሚያስደፍር አይመስለኝም። (ገፅ 111-112)

## 🕮✍ ከኢትዮጵያ ምን ዐይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል? (ግንቦት 1966 ዓ.ም)

መቼም ለውጥ የፍጥረት ሕግ ስለሆነ ዛሬ ባይሆን ነገ ለውጥ መምጣቱ አይቀርም። ጥያቄው "ለውጥ በሰላም? ወይስ ለውጥ በደም?" ስለሆነና ለውጥ በሰላም ሊሆን ሲችል ለውጥ በደም እስኪሆን መጠበቅ ሁሉን ከመጉዳት በቀር ማንንም ስለማይጠቅም ለውጥ በሰላም የሚሆንበትን መንገድ አሁን፣ ጊዜው ሳያልፍ ማበጀት አስፈላጊ ነው . . . . (ገፅ1-11)

በየትም ቢሆን ሁልጊዜ ባለም ታሪክ ሞልቶ የሚታየው አንድ ሕዝብ የሚኖርበት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚክና የማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታ ደስ የማያሰኘው ሲሆንና እንዲያ ያለውን ሁኔታ የሚያሻሽልበት ሰላማዊ መንገድ የማይከፍትለት

ሲሆን ከዚያ ከማይወደው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚክና የማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታ በኃይል ሰብሮ ለመውጣት ሲነሣ፣ በዚያ ምክንያት አገርን የሚያደኸይና የሚያሳዝን የሕይወትና የሀብት ጥፋት ሲደርስ፣ ከዚያ በኋላ የመጨረሻ ለውጥ ሲመጣ ነው:: ነገር ግን ለዚያ ሕዝብ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚክና የማኅበራዊ ኑሮው ስሜቱን እየተከተለ፣ ወይም ከስሜቱ እየቀደመ የሚሻሻልበት ሰላማዊ መንገድ የተከፈተለት እንደሆነ ለውጡ ሽብር ሳይነሣ፣ ሕይወትና ሀብት ሳይጠፋ፣ የታሪክና የመልካም ባህልን መሠረት ሳይለቅ፣ በፀጥታ ሲፈፀም ይታያል:: (ገፅ 2)

በኔ አስተያየት ዛሬ ለኢትዮጵያ በጣም የሚያስፈልገው ኢኮኖሚዋን አፋጥኖ አልምቶ በጠቅላላ የሕዝብዋን የኑሮ ደረጃ ማሻሻልና ያስተዳደርዋን ሆነ የፍርድ ሥራትዋን ለዘመናዊ ኑሮ እንዲስማማና ልማቱን እንዲረዳ ማድረግ ነው እንጂ የምዕራብን፣ ወይም የምሥራቅን ያስተዳደር ሥራት እንዲሁ እንዳለ ተውሶ መልበስ ምሥራቅን፣ ወይም ምዕራብን ሊያደርጋት አይችልም:: ስለዚህ ያቀረብነው አሳብ ከምዕራብና ከምሥራቅ የመንግሥት ሥሪቶች ለኢትዮጵያ ዘመናዊ አስተዳደርና ልማትዋን ለማፋጠን ይረዳሉ ተብሎ የሚታመንባቸው አሳቦች ተዋጥተው ያሉበት፣ በዚያ ላይ ከኢትዮጵያ ታሪክና ባህል ጋር የሚስማሙ አዳዲስ አሳቦች የተጨመሩበት፣ ዓይነተኛ አላማው ባሥር ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያን በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚክና በማኅበራዊ ኑሮ አሁን ካለችበት ዝቅተኛ ቦታ በኃይል ገፍቶ ወደ ፊት ሊያራምዳት ይችላል ብለን የምናምንበት ነው:: (ገፅ 3-4)

የመንግሥት ሥልጣን በኃይል የሚመሠረተው በኮሎኒ፣ ወይም በቅኝ አገር ነው:: በቅኝ አገር ሕዝቡ ድል ሲሆን ሕጋዊ መብቱንም፥ ፈቃዱንም ከነፃነቱ ጋር አብሮ ስለሚቀማ ሕግም፥ ፈቃድም ሁሉ ያው በኃይል የሚመሠረተው በወራሪው ፈቃድ ብቻ ነው:: በነፃ አገር ግን ለመንግሥት ሥልጣን ሕጋዊ መሠረቱ የጠቅላላው ሕዝብ ፈቃድ ነው:: (ገፅ 8-9)

መንግሥት የሕዝቡን ፍላጎት ተከትሎ እንዲፈጽምና እንዲያስፈጽም ሕዝቡ ራሱ በፈለገው ዓይነት የሚያቋቁመው ድርጅት ነው እንጂ እንዲሁ እምኅበ አልቦ ባለቤቱ ባልታወቀ የምሥጢር እጅ በሕዝብ ላይ የሚፈጠር ፍጡር አይደለም:: በሌላ አነጋገር ሕዝብ የመንግሥት ፈጣሪ፥ መንግሥት የሕዝብ ፍጡር ናቸው::

ስለዚህ ሁልጊዜም ቢሆን ወኪል ከወካዩ በላይ ሊሆን እንደማይችል፣ ወይም ፍጡር ለፈጣሪው ታዛዥ እንጂ ፈጣሪውን አዛዥ ሊሆን እንደማይችል መንግሥትም ለፈጠረውና ለወከለው ለሕዝብ አገልጋይና ጉዳይ ፈጻሚ ነው እንጂ የገዛ ፈቃዱን በሕዝብ ላይ ጥሎ የሚያስፈጽም፣ የፈጣሪው ጌታ አይደለም:: ይህን መሠረት አድርገን ስንነሣ ስላስተዳደርም ሆነ ስለሕዝብ ኑሮ ማሻሻልና ስላገር ልማት፥ ወይም ስለ ማንኛውም ሕዝብ ነክ ጉዳይ ሁሉ

ከማንኛውም በላይ የመጀመሪያው መብትም ሆነ አላፊነት፣ ሥልጣንም የባለቤቱ የሕዝብ ነው ወደ ማለት እንደርሳለን።

"መንግት የሕዝብ እንጂ ሕዝብ የመንግሥት አለመሆኑ" ጥርት ብሎ በማያጠራጥር ሁኔታ መታመን አለበት። ይህ በሕዝብና በመንግሥት መሐከል ላለው ግንኙነት ሥር መሠረት፣ ወይም ግንድ የሆነው ነገር ከታመነ ሌላው ሁሉ የሱ ዘርፍና ቅርንጫፍ ነው። (ገፅ 10-11)

በሕዝብ ምርጫ ሳይሆን እላይ እንደተመለከተው አንዳንድ ጊዜ በሕገወጥ መንገድ በኃይል ሥልጣን የሚይዙት ዲክቴተሮች እንኳዋ "የሕዝብ መብትና ጥቅም ጎደለ" ብለው የሕዝብ ጠበቆች ሆነው፣ ወይም መስለው በሕዝብ ስም ካልሆነ እንዲሁ "ሥልጣን ለኛ ይገባል" ብለው ሥልጣን የሚይዙ ዲክቴተሮች የሉም። ርግጥ ሥልጣን ከያዙና ኃይል ሁሉ በጃቸው ከሆነ በሁዋላ ብቻ መቸም ተቆጣጣሪ የሌለበት ሥልጣን ማወሩና ማደንቆሩ ስለማይቀር ማን፣ ወይም ምን አለብን በማለት ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ የራሳቸውን ጥቅም ሲያስቀድሙና የሥልጣናቸውን ዕድሜ ለማስረዘም ሲሠሩ የሚታዩ መኖራቸው አይካድም። (ገፅ 12-13)

በውነቱ በየክፍሉ የሚኖሩትን የኢትዮጵያ ወገኖች ሁሉ በአካልና በመንፈስ አገናኝተው አንድ የሚያደርጉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚክና የማኅበራዊ ኑሮ ድርጅቶች ገና ሳይፈጠሩ፣ በጠቅላላው ሕዝቡ ስላገር አስተዳደርም ሆነ ስለ ልማት ያለውን መብትና ያለበትን አላፊነት ገና ሳያውቅ፣ በደኅናም ሆነ በችግር ጊዜ ይጠቅመኛል፣ ወይም ያዋጣኛል የሚለውን መንግሥት እየመረጠ ራሱን ማስተዳደር ገና ሳይለምድ፥ እንዲሁ አሁን ባለበት ሁኔታ እንዳለ በመሐከሉ አንድ ላይ አድርገው ካያያዙት መንግግና አፋዊ ክሮች አንዱ፣ ወይም ሁሉ የተበጠሱ እንደሆነ እንደገና ማያያዣ ይጠፋና ከኢትዮጵያ ጠላቶች በቀር ሁሉንም የሚያሳዝንና የሚያፀፅት ጉዳት ሊደርስ ይችላል። (ገፅ 25)

አንደኛ፣ ያገር ልማድና እድገት፣ ወይም ወደኋላ መቅረት፣ በዚያም ምክንያት የሚገኘው ጥቅም፣ ወይም የሚደርሰው ጉዳት ዞሮ ዞሮ የሕዝብ ስለሆነ፣ ለኑሮ ደረጃ እድገቱና ለጠቅላላ ደኅንነቱ፣ እንዲሁም ለታሪኩና ለባህሉ የሚስማማ በመሰለው መንገድ የሚፈልገውን ዓይነት መንግሥት ማቋቋሙ ከሁሉ በላይ መብቱም ሆነ ኃላፊነቱ ለሕዝብ ብቻ መሆኑና ይህም ዛሬ ባለም ሁሉ የታወቀ ስለሆነ፣ ዓለም ሁሉ የሚሠራበት መሆኑ የተቻለውን ያህል ባጭሩ [በዚህ መፅሐፍ ውስጥ] ተገለጸ። (ገፅ 46-47)

. . . ነፃ የዜና መንዣ (ፕሬስ) ካለም ጋር መገናኛ በር ከመሆኑም በላይ የሕዝብን ጠቅላላ ስሜት ለመንግሥት፣ የመንግሥትን ሥራና የሥራ ዕቅድ ለሕዝብ የሚያሳይ ሰፊ መስታዋት እንደመሆኑ መጠን፣ መንግሥትንና ሕዝብን

ባካልና በመንፈስ የሚያስተያይና የሚያስተዋውቅ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው። በዘመናዊ ኑሮ ነፃ የዜና መንገዶ የሌለበት አገር ሕዝቡና መንግሥቱ በሚገባ ሊተዋወቁ ስለማይችሉ፣ ሊተማመኑም፣ ሊተባበሩ አይችልም። (ገፅ 49-50)

. . .በልማት ሥራ ከውጭ አገር ኩባንያዎች ጋር አብሮ መሥራት በገንዘብና በቴክኒክ ዕውቀት በኩል ያለው ጥቅም ከፍ ያለ መሆኑ የማይካድ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ እሱን ተከትሎ የሚመጣው አደጋ ከጥቅሙ የበለጠ ሊሆን ስለሚችል መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ማንም አገር ቢሆን ለኢኮኖሚውና ለማኅበራዊ ኑሮው መሠረትና ድጋፍ ከሆኑት ዋና ዋና ሥራዎች የሚበዙት በውጭ ኩባንያዎችና ሰዎች እጅ ከሆኑ የኢኮኖሚክና የማኅበራዊ ኑሮ ነፃነቱን ብቻ ሳይሆን በመጨረሻ የፖለቲካ ነፃነቱን ጭምር እንደሚያጣ ዛሬውኑ በብዙ አገሮች እናያለን።

ኢኮኖሚው በውጭ ባለገንዘቦች እጅ የተያዘ አገር በስም እንኳዋ ነፃ ቢባል መንግሥቱ ሁልጊዜ፥ ከሁሉ አስቀድሞ የነዚህን የውጭ ባለገንዘቦች ጥቅም የሚጠብቅ ካልሆነ በሥልጣን ላይ አይቆይም። ሁልጊዜም፥ በየትም ቢሆን የሀብታምን ጥቅም ለመጠበቅ መንፈሳቸውን በዋጋ የሚሸጡ ደካሞች ጠፍተው አያውቁም።

ስለዚህ ካንድ ወገን የውጭ ባለገንዘቦች ጥቅማቸውን የሚጠብቅላቸው ሲፈልጉ፣ ከሌላ ወገን ያገሩ ሕዝብ ጥቅሙን የሚጠብቅለት መንግሥት ሥልጣን ለማስያዝ ሲፈልግ በብዙ አገሮች እንደምናየው፣ አገራችን በፀጥታ የልማት ሥራዋን በመሥራት ፈንታ የብጥብጥና የጦር ሜዳ እንዳትሆን፣ ለኢኮኖሚያችንና ለማኅበራዊ ኑሮዋችን መሠረቶች የሆኑትን ሥራዎች ገንዘብ ቢያጥረን ተበድረን፣ የቴክኒክ አዋቂዎች ብናጣ ቀጥረን የተቻለውን ያህል እኛ እንድናለማቸው ያስፈልጋል። (ገፅ 71-71)

## 🕮➘ ከፍቅር እስከ መቃብር (1958 ዓ. ም.)

የቆዬ ልማድ የቆዬ በመሆኑ ሁሉ አይወድቅም፣ ወይም ሁሉ አይያዝም። መልካሙና ጠቃሚው ይያዛል የሚሻሻለው ይሻሻላል ሊሻሻል የማይችለው ይወድቃል። ነገር ግን የሚወድቀው ክፉ ልማድ ከስራ ይወገዳል እንጂ ከታሪክ ጸሀፊዎች መጽሐፍና ከደራሲዎች ድርሰት ሊወገድ አይገባውም። ያለዚያ በየጊዜው የሚደረገው የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚክ ወይም ያስተዳደርና የማህበራዊ ኑሮ መሻሻል ከምን ተነስቶ እምን እንደ ደረሰ ሊታወቅ አይቻልም። (ገፅ 10)

የማህበራችን አቁዋም የተሰራበት ስራት ልማዱ፥ ወጉ ህጉ እንደህይወታዊ ስራተ ማህበር ሳይሆን ህይወት እንደሌለው የደንጋይ ካብ አንዱ ባንዱ ላይ ተደራርቦ የላይኛው የታችኛውን ተጭኖ የታችኛው የላይኛውን ተሸክሞ እንዲኖር ሆኖ የተሰራ በመሆኑ ከጊዜ ብዛት የታችኛው ማፈንገጡ ስለማይቀርና ይህ ሲሆን ህንፃው በሙሉ እንዳይፈርስ እንደገና ተሻሽሎ ሰውን ከደንጋይ በተሻለ መልክ የሚያሳይ የህያዋን አቁዋመ ማህበር እንዲሰራ ያስፈልጋል፡፡ (ገፅ 122)

. . .ገበሬ ይዘራል፤ የዘራውም ዘር አበቃቀሉን አሳምሮ ይወጣል፤ ያድጋል፤ ይለመልማል፤ ያብባል፤ ያምራል፤ ዘሪውም ከቡቃያው እስካበባው ድረስ ደስታው ካዝመራው ጋር አብሮ ያድጋል፡፡ ከዚያ ፍሬውን ለማየት በናፍቆት ሲጠባበቅ በመሀከሉ ድንገት አንድ የመርዶ ነቢይ ይመጣና "የዘራኸው ፍሬ አያፈራም ባበባው ደርቆ፥ ገለባ ትቢያ ሆኖ ይቀራል፤ ያንተም ደስታ ከቡቃያ እስካበባው በማየት ብቻ ይወሰናል" ብሎ ቢያረዳው ያ ገበሬ ምን ያክል ይሰቀቅ? ምን ያክል አንጀቱ ይቆረጥ ይሆን?. . . (ገፅ 41)

እየውልህ! ቤተ እግዚአብሔራችን እንደነዚህ ላሉት ሽፍቶች እንደነዚህ ላሉት ዘራፊዎች ዋሻ ሆነች! እየውልህ! ከካህናቶቻችን ከህዋሪያዎቻችን የሚበዙት ካለቆች ጀምሮ በመነኮሳቱ አልፎ እስከ ተራ ደብተሮች እስከ ዲያቆናቱ ድረስ አንዱ አስማት አድራጊ፥ አንዱ አስማት ፈቺ፥ ሌላው ጋኔን ስቦ አምጪ፥ ሌላው ምህረት አሰጪ ነን እያሉ ውሸታቸውን በዬጥምጥማቸው በዬቆባቸው፥ በዬደበሎዋቸው ሸሽገው ሊመሩት፥ ሊያስተምሩት በተሰጣቸው መንጋ የሚጫወቱ ናቸው! ታዲያ ከነዚህ ጋር ማህበርተኛ ሆኖ ባንድ ስመ እግዚአብሄርን መጥራት በተቀደሰ ስሙ ማፌዝ አይደለም?" (ገፅ 428)

## 🕮➾ ከየልምዣት (1980 ዓ. ም.)

. . . ሆዴ የራሱን መሙላት እንጂ የኔን ውርደት፥ የኔን ማዘንና መበሳጨት ከጉዳይ የማይጽፍ መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ስለዚህ፥ 'ለካስ ሆዴና እኔ ልዩ ነን፡፡ ለካስ ሆዴ የኔ ሲመስለኝ ባዕድ ነው' ብዬ ታዘብሁት፡፡ (ገፅ 180)

ትምህርት ሰፊ ነው፤ በሱ መጠን ጥበብ ጠባብ ነው፡፡ ትምህርት ለሰው ሁለተኛ ፈጣሪው፥ ጥበብ መሣሪያው ናቸው. . . ሰው በትምህርት ያደረጉትን ሁሉ ይሆናል፡፡ በጥበብ መሣሪያነት እሱነቱን ሳይተው፥ ኑሮውን፥ ሕይወቱን ያሻሽላል፥ ያሳምራል፡፡ ስለዚህ፥ የዛሬው ትውልድ ትምህርት ቤት ተከፍቶለት እዚያ ያገኘውን እንዲማርና የተማረው ያደረገውን ሁሉ እንዲሆን ስለተፈረደበት የተማረው ያደረገውን ሆነ . . . የተማረው ምንድነው? የፈረንጅ የሆነውን ሁሉ የሚያስመኝ!

ዛሬ፥ የፈረንጅ ትምህርት በተማረውም ሆነ፥ ከተማረው በቀላወጠው ጥራዝ ነጠቅ መሐከል፥ ኢትዮጵያዊ ላለመምሰልና ፈረንጅ ለመምሰል፥ ልብ እስኪወልቅ ትንፋሽ እስኪረቅ፥ ያለውን ሩጫ፥ ያለውን ቅድድም እናውቃለን:: (ገፅ 373)

'መሆን በድል፥ መምሰል በትግል፥ ያውም በከፊል' [እንደሚባለው] . . . መምሰል በጣም አድክሞ፥ በጣም አክስሮ፥ ለመምሰል የሚፈልገውን በሙሉ መምሰል ምንም ቢሆን የማይቻል ነው::

ጥበብ ግን፥ አንድ ጊዜ አንድ አገር ይፈጠር እንጂ፥ በዘር በባህል፥ በወግ በሥራት፥ በምንት በስሜት የማንም ያልሆነ፥ የሁሉም የሆነ በመሆኑ፥ 'ጥበባቸውን አንቅዳ' [አልተባለም]:: ፈረንጆች ራሳቸው፥ እያንዳንዳቸው የሚፈጥሩትን አዳዲስ ጥበብ እስበሳቸው እንደሚቀዳዱ የታወቀ ነው:: ብቻ፥ ሁሉም የየራሳቸውን የተፈጥሮ የጸጋ መለያ እንደያዙ፥ ሁሉም የየራሳቸውን እነሱነት ሳይለቁ ነው!! (ገፅ 375)

ፈረንጆች፥ በውቀት ይሁን በስተት - በየትኛው መሆኑን እግዜር ይወቀው - የሚጽፉት ሆነ የሚያስተምሩት፥ ፈረንጅን እና የፈረንጅ የሆነውን ሁሉ የሚያስወድድ፥ የሚያስደንቅ፥ የሚያስመኝ፥ ሌሎችንና የሌሎች የሆነውን ጭምር አዋርዶ፥ አጎሳቁሎ የሚያሳይና የሚያስንቅ፥ የሚያስጠላ፥ የሚያስጸይፍ ነው::

ታዲያ እንግዲያ፥ ከሕፃንነታቸው ጀምረው እንዲያ ያለውን ትምርት ብቻ በትምርት ቤት እዬተማሩ የሚያድጉ ልጆች፥ እንዲያ ያለው ትምርት እውነት አለመሆኑን የሚያስረዳ ማረሚያ ማስተባበያ፥ ማስተሀቀሪያ በመስጠት ፈንታ፥ በሱ ለላቁ ሽልማት እየሰጠን . . . በሱ እንዲመሩ እያደፋፈርን የምናሳድጋቸው ልጆች . . . በጠቅላላው የራሳቸው የሆነውን ሁሉ የሚንቁና የሚጠሉ . . . በጠቅላላው የፈረንጅ የሆነውን ሁሉ የሚወዱ፥ የሚያደንቁና የሚመኙ መሆናቸው የማይቀር ነው:: (ገፅ 381)

## ስለጽሑፍ አቅራቢዎቹ፥ መግለጫ
## (NOTES ON CONTRIBUTORS)*

*አስፋው ዳምጤ፤* በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች፥ እንዲሁም በሬዲዮና በቴሌቪዢን አማካይነት የሥነ ጽሑፍና የኪነ ጥበብ ተቺና አሐዛቢ ነው:: አስፋው *አንድ ለአምስት* በሚል ርእስ በጻፈው ልብ ወለድ ታሪክ የታወቀ ደራሲ ነው::

*ብርሃኑ ገበየሁ፤* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ሙሉ መምህር (ሌክቸረር) ነው::

*ዮናስ አድማሱ፤* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ነው::

*ፈቃደ አዘዘ፤* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር ነው:: ፈቃደ፥ ሦስት የግጥም መድበሎችን (*ጨኸት፤ እየሄድኩ አልሄድም* እና *አያ ጎሸሜ*) እና ሁለት መጻሕፍትን (*የሥነ ቃል መምሪያ* እና *Unheard Voices*) ያሳተመ ደራሲ ነው::

---

(*የጽሑፍ አቅራቢዎቹ ዝርዝር የቀረበው ያቀረቧቸው ጽሑፎች በዚህ እትም ውስጥ በወጡበት ቅደም ተከተል ተራ ነው:: በዚህ አጋጣሚም፥ ወደፊት ለመጽሔታችን ጽሑፍ የሚያቀርቡ ሰዎች፥ በተለይ ደግሞ ከዩኒቨርሲቲው ውጭ የሆኑት፥ ስለትምህርት ደረጃቸው፥ ስለሙያቸው፥ ስለሚሠሩበት ተቋም አጭር መግለጫ እንዲልኩልን ለማሳሰብ እንወዳለን::)

## GUIDELINES FOR CONTRIBUTORS*

***Manuscripts*:** Materials should be typed double-spaced, on A-4 paper, with 1.25-inch margins on all sides, and should be submitted in two copies. Manuscripts should not exceed 30 pages and they should have a separate title page with the author's name, institution and mailing address. The first page of the manuscript should also have the title of the article and the name of the author. An abstract of not more than 300 words should also bè submitted along with the manuscript.

***Organization of Text*:** Manuscripts should be divided into sections and sub-sections, each indicated by numerals, as in the following:

1. Section
1.1. Sub-Section
1.1.1. Sub-Sub-Section, etc.

***Tables and Figures*:** Tables and figures shoud be identified by numerals and should fit into the page in columns with plenty of space between the columns.

***Footnotes*** Footnotes should be numbered consecutively in the order they appear in the text, and they must be typed single-spaced on a separate page. They should be used sparingly for illustrating and elaborating points that are relevant, but not central, to issues discussed in the text. They should not be used for citing references.

***References*:** References should be presented on a separate page, typed in alphabetical order, single-spaced (double space between entries) in accordance with the following format:

---

* ***These guidelines are subject to change as conditions may necessitate.***

Leslau, W. 1968. "The Expression of the Future in the Ethiopian Languages." *Journal of African Languages.* 7:1, 68-72.

_____. 1982. *Gurage Folklore.* Wiesbaden: Franz Steiner Verlag.

Kempson, R. 1979. *Semantic Theory.* Cambridge: Cambridge University Press.

When citing references in the text, the last name only of the author should be used, followed by the date of publication in parentheses. Example: Chomsky (1981) or Chomsky (1981:122).

***Editorial Procedure:*** Receipt of manuscripts will be acknowledged. Manuscripts will then be reviewed by at least two readers, and a decision will be made on consideration for publication. Accepted or not, manuscripts will not be retured to authors unless pre-paid, self-addressed envelopes are provided by the authors at the time of submission. Authors whose articles are published will receive a free copy of *the issue of the Journal in which their articles have apperred.*